# የጥላቻ ንግግር ህግ አዋጅና እድምታዎቹ

## መግቢያ

የኢትዮጵያ መንግስት በአገሪቱ ያለዉን አለመረጋጋት ለመቆጣጠር ያስችለኛል ያለዉን የጥላቻ ህግ ረቂቅ አዋጅ ይፋ በማድረግ ህጉን በማፅደቅ ተግባራዊ ለማድረግ በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል። አገሪቱ ዉስጥ ያለዉ የፖለቲካ አለመረጋጋት መፍትሄ የሚሻ ጉዳይ መሆኑ አከራካሪ አይደለም። ዶ/ር አብይ ወደ ስልጣን ከመጡበት መጋቢት 24 2010 ዓ.ም ጊዜ ጀምሮ አግሪቱ በከፍተኛ የፖለቲካ ለዉጥና ነዉጥ ዉስጥ ትገኛለች። ለዉጡን ተከትሎ የመጣዉ የፖለቲካ ምህዳሩ መከፈት ግለሰቦች፥ የብሄር ድርጅቶችና ሚድያዎች ሃሳባቸዉን በአንፃራዊ ነፃነት የሚገልፁበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። የአገሪቱ የፖለቲካ አወቃቀር ብሄርን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የፖለቲካ ምህዳሩ መከፈት ተከትሎ ብሄር ተኮር የፖለቲካ ሃይሎች በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ተጠናከረዉ በመዉጣታቸዉ የብሄር ግጭት፥ መፈናቀል፥ ዝርፊያና አለመረጋጋት በተለያዩ አካባቢዎች ተከስቷል።[1] በቅርቡ በአማራና በደቡብ ክልሎች የተከሰቱትን ግጭቶች ተከትሎ መንግስት የሃይል እርምጃ በመዉሰድ ብዙዎች ለእስር ተዳርገዋል። [2] መንግስት ከፍተኛ ተቃዉሞ የቀረበበትን የ ፀረ ሽብርተኝነት ህጉን በመጠቀም የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች ላይ ክስ ማቅረቡ ለዉጡ እየተቀለበሰ ነዉ የሚል ስጋት አድሮባቸዋል። አገሪቱ ዉስጥ ካለዉ ዘርን መሰረት ባደረገዉ የፖለቲካ ስርአት ምክንያት የዘር መከፋፈልና ጥላቻ እየተስፋፋ በመምጣቱ የጥላቻ ህግን ማዉጣት በመርህ ደርጃ አስፈላጊ ቢሆንም የህጉ መዉጣት የሚያስከትለዉን ችግር ማንሳት አስፈላጊ ነዉ። ይህ ፅሁፍ የጥላቻ ህግ ታሪካዊ አመጣጥ ፥ አለም አቀፍ ልምዶችና በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ባለዉን ህገ መንግስታዊ ስርአትና ፖለቲካዊ ሁኔታ አንፃር በመዳሰስ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለመጠቆም ይሞክራል።

## 1. የጥላቻ ህግ ታሪካዊ አመጣጥና አለም አቀፍ ልምዶች

የጥላቻ ህግ ታሪካዊ አመጣጥ ሃሳብን በነፃነት ከመግለፅ ጋር በቅርብ የተቆራኘ ነዉ። ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት በጥንታዊ አቴንስ ከክርስቶስ ልደት በፊት በስድስተኛዉ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ትኩረት ያገኘ መሰረታዊ መብት ነዉ። ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት በ17ኛዉ ክፍለ ዘመን በነበረዉ የእንግሊዝ የመብት ትግል እንዲሁም እ.ኤ.አ. በ1789 ዓም በፈረንሳይ አብዮት ወቅት የወጣዉ የሰዉ ልጆች መብት ድንጋጌ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ትልቅ ዋስትና ሊኖረዉ የሚገባ ጉዳይ መሆኑን አፅኖት አድርጎበታል። እ.ኤ.አ. በ 1789 ዓም የወጣዉ የአሜሪካ ህገ መንግስት የመጀመርያዉ ማሻሻያ ( First Amendment)

---

[1] Ethiopia: 3 million internally displaced in escalating humanitarian crisis, https://www.euronews.com/2019/01/31/ethiopia-3-million-internally-displaced-in-escalating-humanitarian-crisis

[2] In era of reform, Ethiopia still reverts to old tactics to censor press, https://cpj.org/blog/2019/07/ethiopia-coup-internet-censored-blocked-jailed-journalists.php

የአሜሪካ ም/ቤት ሃሳብን የመግለፅ ነፃነትን የሚገድብ ምንም አይነት ህግ ማዉጣት እንደማይችል በመደንገግ የንግግር ነፃነት በአሜሪካ ማህበረሰብና በአለም አቀፍ ደረጃ ገደብ እንዳይደረግበት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዲኖረዉ አድርጓል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.አ. 1945 ዓም ከተመሰረተበት ወቅት ጀምሮ ትኩረት ያገኘዉ የሰብአዊ መብት ጥበቃ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅን መብት በአለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት እንዲያገኝ አድርጎታል። እ.ኤ.አ. በ 1948 ዓም የወጣዉ አለም አቀፉ የሰብአዊ መበት ድንጋጌ
( Universal Declaration of Human Rights) በአንቀፅ 19 ላይ እንዳስቀመጠዉ ማንኛዉ ሰው ሃሳቡን በነፃነት የመግለፅና የማሰራጨት ያለገደብ መብት እንዳለዉ አረጋግጧል። እንዲሁም እኤአ በ 1966 ዓም የወጣዉ አለም አቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ድንጋጌ ( International Covenenat on Civil and Poltical Rights) አንቀፅ 19 ላይ የተቀመጠዉ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት አሁን በአለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት ላጋኘዉ ህሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት እንቅስቃሴ መሰረት ጥሎአል። የቀዝቃዛዉን ጦርነት ማብቃት ተከትሎ በጭቆና ስር የነበሩት ታዳጊ አገሮችም ሳይቀሩ ሀሳብን በነፃነት መብትን እውቅና የሚሰጥ የህገ መንግስትና የፖለቲካ ስርአት ደንግገዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከሰቱ አለም አቀፍ ሁኔታዎች የጥላቻ ንግግር እንዲስፋፉ ምክንያት እንደሆኑ ይታመናል። ሉላዊነት ( globalaization) በአሜሪካና አዉሮፓ በሃብታምና ድሃዎች መካከል የፈጠረዉ ልዩነትና ስደተኞች ያለ ገደብ ድንበር አቋርጠዉ መግባታቸዉ በስደተኞች ላይ ጥላቻን መሰረት ያደረጉ ወንጀሎች እንዲስፋፉና ቀኝ አክራሪ ብሄርተኛ ፖለቲከኞች የፖለቲካ ስልጣን እንዲይዙ ምክንያት ሆነዋል። ከዚህም በተጨማሪ በድህረ ገፆችና ማህበራዊ ሚድያዎች የሚሰራጩ የጥላቻ ንግግሮችና ሀሰተኛ ወሬዎች ( fake news) በከፍተና ደረጃ በመጨመሩ መንግስታት ይህንን አካሄድ ለመቆጣጠር ከፍተኛ ሙከራ እያደረጉ ነዉ። ከቅርብ አመታት ወዲህ የመገናኛ ብዙሃን ቴክኖሎጂ በከፍተኛ ሁኔታ በማደጉ ምክንያት ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት በከፍተኛ ደረጃ እድገት አሳይቷል።

በተለይም ደግሞ በኢንተርኔት ቴክኖሎጂ እድገት ምክንያት የመረጃ አቅርቦትና ስርጭትን ታላቅ እምርታ የታየበት ሲሆን ማህበራዊ ሚዲያዉ መደበኛ የመገናኛ ብዙሃንን በመተካት ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ ነፃነትን አስገራሚ በሆነ ሁኔታ ቀይሮታል። አለማችንን ያስተሳሰረዉ የቴኖሎጂ እድገት ግን የራሱን ችግሮች ይዞ ብቅ ብሎአል። የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም የሚፈፀሙ የሽብርና የጥላቻ ንግግሮች የፈጠሩት ተፅእኖ ቴክኖሎጂዉን ለመቆጣጠር አቅም የሌላቸዉን ብቻ ሳይሆን በቴክኖሎጂ የበለፀጉትንም አገራት ስጋት ላይ ጥሎአል። ይህ ችግር በተለይ በታዳጊ አገሮች ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ ይገኛል። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ለዘመናት በጭቆና ዉስጥ ያሉ አገሮች ማህበራዊ ሚድያዉ ከፍተኛ የመረጃ ምንጭ ተደርጎ ስለሚቆጠር የራሱ በጎ ቢኖረዉም የጥላቻና ሃሰተና ወሬዎች በማሰራጨትና ከፈተኛ ችግር ይፈጥራል። በአደጉትም ሆነ በታዳጊ አገሮች በማህበራዊ የትስስር መድረኮች የሚተላለፉ የጥላቻ ንግግሮች ስደተኞችንና በቀለም ወይም በዘር ከህብረተሰቡ ለየት ያሉ ግለሰቦች ለጥቃት እንዲጋለጡ ማድረጉን ጥናቶች አረጋግጠዋል።[3] በተለይ በአዉሮፓና አሜሪካ ቀኝ ዘመም የፖለቲካ መሪዎች ወደ ስልጣን መምጣት ብሄረኝነትንና ዘረኝነትን አልፈዉታል የሚባሉትንም ዴሞክራሲያዊ ስርአት የገነቡትን አገሮችንም

[3] Hate Speech on Social Media: Global Comparisons, https://www.cfr.org/backgrounder/hate-speech-social-media-global-comparisons

የጥላቻ ንግግር እየናጣቸዉ ይገኛል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በቅርቡ በአወጣዉ መግለጫ ፀትላቻ ንግግሮች በለም ዙርያ በከፍተኛ ደረጃ እያደጉ መምጣታቸዉን በመግለፅ ይህን ለመቋቋም የሚያስችል የድርጊት መርሃ ግብር ቀይሷል።[4]

ምንም እንኳን የጥላቻ ንግግር በአለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት እያገኘ ቢመጣም የጥላቻ ንግግር ምን ማለት እንደሆነ የሚያስረዳ አለም አቀፍ ስምምነት ግን የለም። የአዉሮፓ ም/ቤት ያወጣዉ አንድ ሰነድ የጥላቻ ንግግርን ማንኛዉም ዘርን ፥ የዉጭ አገር ዜጎችን፥ አይሁዳውያንን አስመልክቶ የሚያሰራጭ፥ የሚያነሳሳና የሚያስፋፋ ማንኛዉም ሃሳብን የመግለፅ መንገድ በተለይም ህዳጣንንና ስደተኞችን የሚያገል ፅንፈኛ ብሄርተኝነት፥ አድልዎና ጥላቻ የሚያካትት መሆኑን ይገልፃል።[5] አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች የጥላቻ ንግግር ምን እንደሆነ ግልፅ ትርጉም ባይሰጡም ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት የጥላቻ ንግግሮች ለመቆጣጠር ገደብ ሊጣልበት እንደሚችል ይደነግጋሉ። እ. ኤ. አ. በ1966 ዓም የወጣዉ አለም አቀፉ የሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች ስምምነት ሃሳብን በመነፃነት የመግለፅ መብትን መሰረታዊ የሰብአዊ መብቶች አካል አድርጎ ቢቀበለዉም ማንኛዉም የብሄርን፥ የዘርና የሃይማኖት ጥላቻ የሚያስፋፋ ንግግር መድልዎን፥ ጥላቻንና ጥቃትን የሚያነሳሳ ስለሆነ በህግ እንደሚከለከል ይደነግጋል።[6]

እ.ኤ.አ. በ 1965 የወጣዉ አለም አቀፉ የፀረ መድልዎ ስምምነት ማንኛዉንም የዘር የበላይነትን፥ ጥላቻንና የዘር መድልዎን ወይም ጥቃት እንዲደርስ የሚገፋፉ ማንኛዉንም ግግሮችን ማሳራጩት በወንጀል እንዲቀጡ አባል አገራትን ያሳስባል ። [7]

የዴሞክራሲያ ስርአት አገሮች የጥላቻ ህግን የሚያስተናግዱበት መንገድ ይለያያል። በተለይም የዴሞክራሲያዊ ስርአት በሚከተሉት አሜሪካንና አዉሮፓ አገሮች የጥላቻ ህግን አስመልክቶ ያላቸዉ ልምድ በእጅጉ ይለያያል። በሁለተኛዉ የአለም ጦርነት ወቅት ናዚ ጀርመን በአይሁዳዉያን ላይ በፈፀመዉ ጥላቻን መሰረት ያደርገ ዘር ማጥፋት ወንጀል ምክንያት በአዉሮፓ የንግግር ነፃነትን የሚገድብ ጠንከር ያሉ የጥላቻ ህጎች ወጥተዋል። ዴንማርክ፥ ፈረንሳይ፥ ኔዘርላንድና እንግሊዝን በመሳሰሉት አገሮችም ማንኛዉም ዘርን፥ ሃይማኖትንና ፆታን መሰረት ያደርገ የጥላቻ ንግግርም ሆነ ስድብ የተከለከለ ነዉ። በአዉሮፓ ዉስጥ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት እዉቅና ያለዉ ቢሆንም በርካታ ገደቦች ይጣሉበታል። ከጦርነቱ ማብቃት በሁዋላ የአዉሮፓ አገሮች የተስማሙበትና እ.ኤ.አ. በ1950 ዓም በአዉሮፓ ም/ቤት የፀደቀዉ የአዉሮፓ የሰብአዊ መብት ስምምነት

---

[4] UN Warns of Global " Groundswell" Hate Speech, https://www.cbsnews.com/news/un-secretary-general-antonio-guterres-warns-of-global-groundswell-of-hate-speech/

[5] Recommendation (97)20 of the Council of Europe, 30 October 1997 - "the term 'hate speech' shall be understood as covering all forms of expression which spread, incite, promote or justify racial hatred, xenophobia, anti-Semitism or other forms of hatred based on intolerance, including: intolerance expressed by aggressive nationalism and ethnocentrism, discrimination and hostility against minorities, migrants and people of immigrant origin".

[6] Article 20 (2) of the International Covenant on Civil and Political Rights (ICCPR) states: Any advocacy of national, racial or religious hatred that constitutes incitement to discrimination, hostility or violence shall be prohibited by law.

[7] Article 4, International Convention on the Elimination of Racial Discrimination, 1965 States "shall declare an offence punishable by law all dissemination of ideas based on racial superiority or hatred, incitement to racial discrimination, as well as all acts of violence or incitement to such acts against any race or group of persons of another colour or ethnic origin, and also the provision of any assistance to racist activities, including the financing thereof"

ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን እውቅና ቢሰጥም ገደብ ሊጣልባቸዉ የሚቻልበትን ምክንያቶች ይዘረዝራል። [8] በዚህም መሰረት ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት የዴሞክራሲ ስርአት ለመገንባት፣ ለብሄራዊ ደህንነት፣ የሃገር አንድነትና የህዝብ ደህንነት ለመጠበቅ፣ ሁከትን ወይም ወጀልን ለመከላከል፣ የህዝብን ጤና ወይም ግብረገብነትን ፣ የሌሎች ሰዎችን ክብርና ደህንነት ለመጠበቅ በህግ ገደብ ሊጣልበት ይችላል። [9] ይህንንም ድንጋጌ መሰረት በማድረግ በርካታ የአዉሮፓ አገሮች የጥላቻ ህግን የሚቆጣጠር ህጎችን አዉጥተዋል። ሌሎች የአዉሮፓ አቀፍ ተቋማትም የጥላቻ ህግን በማስመልከት በርካታ ህግጋትን ደንግገዋል። የአዉሮፓ ም/ቤት የሚኒስትሮች ኮሚቴ ያወጣዉ የጥላቻ ንግግር ትርጉም ሰፋ ያለ ዝርዝር ያለው ነዉ። ኮሚቴዉ የጥላቻ ንግግርን ማንኛዉም የዘር ፣ የዉጭ ዜጎችን፣ ፀረ ሴማዊነት ጥላቻን የሚያንሳሳ፣ የሚያሰራጭና የሚያስፋፉ ንግግር ወይም መቻቻልን የሚፃረር ፅንፈኛ የሆነ ብሄርተኝነት እንዲሁም የህዳጣንንና ስደተኞችን መድልዎና ጠላትነት የሚያስፋፉ ንግግርን ያጠቃልላል። [10] የአዉሮፓ ፀረ ዘረኝነት ኮሚሽን ምክረ ሃሳብም የጥላቻ ንግግርን ምንነት በእጅጉ በመለጠጥ ማንኛዉንም ግለሰብ ወይም ቡድን ዘር፣ ፆታ፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ መለያ መሰረት በማድረግ የሚደረግ ስድብ፣ ማንቋሸሽና አሉታዊ ንግግር ሁሉ የጥላቻ ንግግር ተደርጎ እንደሚቆጠር ይገልፃል። [11] የአዉሮፓ ህብረት ምክረ ሃሳብ የዘር ፍጅት መካሄዱን መካድ ፣ ማጣጣል ወይም መደገፍን አባል ሃገራት እንደ ጥላቻ ንግግር በመቁጠር በወጀለኛ ህጋቸው ዉስጥ እንዲያካትቱ ያሳስባል።[12]

[8] "Everyone has the right to freedom of expression. This right shall include freedom to hold opinions and to receive and impart information and ideas without interference by public authority and regardless of frontiers. This Article shall not prevent States from requiring the licensing of broadcasting, television or cinema enterprises," Art 10(1) European Convention on Human Rights, 1950.

[9] "The exercise of these freedoms, since it carries with it duties and responsibilities, may be subject to such formalities, conditions, restrictions or penalties as are prescribed by law and are necessary in a democratic society, in the interests of national security, territorial integrity or public safety, for the prevention of disorder or crime, for the protection of health or morals, for the protection of the reputation or rights of others, for preventing the disclosure of information received in condence, or for maintaining the authority and impartiality of the judiciary," Art 10(2), ECHR.

[10] Committee of Ministers of the Council of Europe Recommendation No R 97(20) 30.10.1997 on "hate speech" "All forms of expression which spread, incite, promote or justify racial hatred, xenophobia, antisemitism or other forms of hatred based on intolerance, including: intolerance expressed by aggressive nationalism and ethnocentrism, discrimination and hostility against minorities, migrants and people of immigrant origin"

[11] European Commission against Racism and Intolerance (ECRI), General Policy Recommendation No 15 on "hate speech" 8.12.2016 "the use of one or more particular forms of expression – namely, the advocacy, promotion or incitement of the denigration, hatred or vilification of a person or group of persons, as well any harassment, insult, negative stereotyping, stigmatization or threat of such person or persons and any justification of all these forms of expression – that is based on a non- exhaustive list of personal characteristics or status that includes "race", colour, language, religion or belief, nationality or national or ethnic origin, as well as descent, age, disability, sex, gender, gender identity and sexual orientation"

[12] Council framework decision on "combating certain forms and expressions of racism and xenophobia by means of criminal law" 2008/913/JHA, 28.11.2008

በአንዳንድ የአዉሮፓ አገሮችን ያለዉን የጥላቻ ህግ መዳሰሱ በአዉሮፓ ዉስጥ ያለዉን ሁኔታ ለመረዳት ያስችላል። ጀርመን በሁለተኛዉ የአለም ጦርነት ከደረሰባት ከፍተኛ ዉድቀት የተነሳ ጠንካራ የሚባል የጥላቻ ህግ አውጥታለች። በጀርመን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ማንኛዉም ሰዉ የህዝብን ሰላም ለማወክ አንድን የብሄር፥ ዘር፥ ሃይማኖት ማህበረሰብ ወይም ግለሰቦችን ያላቸዉን ሃይማኖት ወይም ዘር መሰረት በማድረግ የጥላቻ ቅስቀሳ ያደረገ ወይም እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎችን ክብር የሚነካ ስድብና ማዋረድ ያደረገ ከሶስት ወር እስከ አምስት አመት እስራት ያስቀጣል።[13] ጀርመን ዉስጥ የናዚን ምልክት ማሳየት ወይም በአይሁዳዉያን ላይ የደረሰዉን የዘር እልቂት መካድም እንደ ጥላቻ ወንጀል በመቆጠር ያስቀጣል።

ከዚህ ባለፈ ጀርመን በቅርቡ ያወጣችዉ በኢንተርነኔት የሚተላለፉ የጥላቻ ወይም ህገወጥ  መልእክቶችን የሚቆጣጠር አዋጅ የማህበራዊ የትስስር መረብ ባላቤቶች ህገወጥ የሆኑ መልእክቶችን በአጭር ጊዜ ዉስጥ ካላነሱ ድርጅቶች በሚልዮን ዶላር የሚቆጠር ቅጣት እንዲጣልባቸዉ ያዝዛል።[14] የጀርመን ወንጀለኛ መቅጫ ህግ የጥላቻን ህግ ከመከልከል ባለፈ 'ኢ ህገ መንግስታዊ' የፖለቲካ ድርጅቶችን አርማዎችና ምልክቶች  በአደባባይ መያዝን ህገ ወጥ በማድረግ በተለይ የናዚ ፓርቲ መለያዎች ለምርምርና ትምህርታዊ  አላማዎች ዉጪ በማንኛዉም መልኩ መጠቀም የተከለከለ የጥላቻ ንግግር አካል አድርጎ ያስቀምጠዋል። ፊንላንድም ማንኛዉም ዘርንና ሃይማኖትን መሰረት አድርገው የሚነዙ የጥላቻ ቅስቅሳዎችን በህግ ከልክላለች።[15] በተለይም የጥላቻ ንግግሩ የዘር ፍጅት እንዲከሰት የሚቀሰቅስ ከሆነ ከበድ ያለ ቅጣትን ያስከትላል።[16] እንግሊዝም በተመሳሳይ

---

13 Incitement of the People (*Volksverhetzung*) is defined by § 130 (Incitement to hatred) Section 1 of the Criminal Code፡

Whosoever, in a manner capable of disturbing the public peace:

1. incites hatred against a national, racial, religious group or a group defined by their ethnic origins, against segments of the population or individuals because of their belonging to one of the aforementioned groups or segments of the population or calls for violent or arbitrary measures against them; or
2. assaults the human dignity of others by insulting, maliciously maligning an aforementioned group, segments of the population or individuals because of their belonging to one of the aforementioned groups or segments of the population, or defaming segments of the population,

shall be liable to imprisonment from three months to five years.

[14] Germany's NetzDG and the Threat to Online Free Speechhttps://law.yale.edu/mfia/case-disclosed/germanys-netzdg-and-threat-online-free-speech

[15] Section 10 - Ethnic agitation (511/2011)

A person who makes available to the public or otherwise spreads among the public or keeps available for the public information, an expression of opinion or another message where a certain group is threatened, defamed or insulted on the basis of its race, skin colour, birth status, national or ethnic origin, religion or belief, sexual orientation or disability or a comparable basis, shall be sentenced for ethnic agitation to a fine or to imprisonment for at most two years.

[16] Section 10(a) – Aggravated ethnic agitation (511/2011)

If the ethnic agitation involves incitement or enticement (1) to genocide or the preparation of genocide, a crime against humanity, an aggravated crime against humanity, a war crime, an aggravated war crime, murder, or manslaughter committed for terrorist intent, or (2) to serious violence other than what is referred to in paragraph 1 so that the act clearly endangers public order and safety, and the ethnic agitation also when assessed as a whole is aggravated, the offender shall *be sentenced for aggravated ethnic agitation to imprisonment for at least four months and at most four years.*[1]

ማንኛዉም ሰዉ ጥላቻን መሰረት ያደረገ የፅሁፍም ሆነ ሌላ አይነት ምልክት በመጠቀም የዘር ጥላቻን ለመቀሰቀስ የሞከረ ከባድ የእስር ጥቃት ያስከትላል።[17] በሁሉም የአዉሮፓ አገሮች የጥላቻ ንግግርን የሚቆጣጠሩ ህግጋት ተግባራዊ ተደርገዋል።

ከአዉሮፓ በተቃራኒዉ በአሜሪካ የጥላቻ ንግግር ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ አካል ተደርጎ ስለሚቆጠር ንግግሩ ብቻዉን አያስቀጣም። በአሜሪካ ዉስጥ ያለዉን ሰፊ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት የመጀመርያዉ የህገ መንግስት ማሻሻያ ተብሎ በሚታወቀዉ ህግ ዋስትና ያገኘ ነዉ። በዚህ ህግ መሰረት የአሜሪካ ኮንግረስ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅን፣ የመሰብሰብንና የእምነት ነፃነትን የሚገድብ ምንም አይነት ህግ ማዉጣት አይችልም።[18] የአሜሪካ ጠቅላይ ፍ/ቤት የጥላቻን ንግግሮችን አስመልክቶ የተለያዩ ዉሳኔዎች የሰጠ ቢሆንም የጥላቻ ህግን እንደ ወንጀል ቆጥሮአቸዉ አያዉቅም። ፍ/ቤቱ እ.ኤ.አ. በ 1969 ዓም በሰጠዉ ዉሳኔ መንግስት የጥላቻ ንግግሩ ረብሻን የመቀስቀስ እድሉ የማይቀር ከሆነ ብቻ መንግስት እንዲህ አይነቱ ንግግር ገደብ ሊጥልበት እንደሚችል ይፈቅዳል።[19] ከዚህ ዉጭ ግን አንድ ንግግር የዘር ጥላቻን የሚመመለከት ነው በሚል ብቻ በህግ አያስጠይቅም። የጥላቻ ንግግር ገደብ እንዲዲደረግበት የሚጠይቁ እንቅስቃሴዎች ቢኖሩም እስከ አሁን የጥላቻ ንግግርን የሚፈቅደዉ ህግ አልተሻሻለም። አሜሪካ ህገ መንግስት ሃሳብን በነፃነት መግለፅ ያለ ገደብ የተጠበቀ በመሆኑ ከጥላቻ ንግግር ( hate speech) ይልቅ የጥላቻ ወንጀል ( hate crime) በህግ ከባድ ቅጣት ያስከትላል። ማንኛዉም የዘር ጥላቻን መሰረት አድርጎ በንብረት ወይም በሰዉ ላይ የሚፈፀም የጥላቻ ወንጀል ተደርጎ ይቆጠራል። [20] በአሜሪካን ህግ አንድ ሰዉ በዘር ወይም ሃይማኖታዊ ጥላቻ ላይ ተመስርቶ የሚፈፀመዉ ማንኛዉም ጥቃት ከፍተኛ የሆነ የወንጀል ተጠያቂነት ያመጣል። የሜሪካን ህግ ከፍተኛ ትኩረት የሚያደርገዉ ከጥላቻ ንግግር ይልቅ የጥላቻ ወንጀሎች በጥብቅ መከታተል ላይ ነዉ ።

## 2. ዘር ተኮር ፖለቲካና የጥላቻ ንግግር

በአለማችን ያሉት ዴሞክራሲያዊ አገሮች መሰረት የሆነዉ ሌብራል አስተሳሰብ ዜጎች ያላቸዉን የሃይማኖትና የዘዉግ ማንነት ወደ ጎን በመተዉ ዜጎች በሰዉነትወይም ዜግነት እኩል መብት እንዲኖራቸዉ በማድረግ ከጎሳና ሀይማኖት ልዩነት ምክንያት ሊፈጠር የሚችለዉን ግጭት በማስወገድ የተረጋጋና የበለፀገ ማህበረሰብ እንዲፈጠር አስችሎአል። አዉሮፓዉያን ለረጅም

---

[17] Public Order Act 1986 prohibits, by its Part 3

A person who uses threatening, abusive or insulting words or behaviour, or displays any written material which is threatening, abusive or insulting, is guilty of an offence if—

(a) he intends thereby to stir up racial hatred, or
(b) having regard to all the circumstances racial hatred is likely to be stirred up thereby.

Offences under Part 3 carry a maximum sentence of seven years imprisonment or a fine or both.

[18] Amendment I፡ Congress shall make no law respecting an establishment of religion, or prohibiting the free exercise thereof; or abridging the freedom of speech, or of the press; or the right of the people peaceably to assemble, and to petition the government for a redress of grievances.

[19] Brandenburg v. Ohio, 395 U.S. 444 (1969)

[20] The FBI has defined a hate crime as a “criminal offense against a person or property motivated in whole or in part by an offender’s bias against a race, religion, disability, sexual orientation, ethnicity, gender, or gender identity.”

ዘመናት በሃይማኖትና ቋንቋ ልዩነት እርስ በርስ በጦርነት ሲታመሱ ከኖሩ በሁዋላ በመጨረሻዉ ብቸኛ መፍትሄ አድርገዉ የወሰዱት ሃይማኖትንና ብሄርን ከፖለቲካ ሂደቱ በማስወጣት በሲቪል ብሄርተኝነት (civic nationalism) ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ስርአት ማካሄድ ነው። በተቃራኒው ከሊብራል ፖለቲካዊ እሳቤ ያፈነገጠዉ ፋሽዝም በሁለተኛዉ የአለም ጦርነት ወቅት የፈጠረው እልቂት፤ አክራሪ ብሄርተኝነት የሚወልደዉ ጥላቻ ምን ያህል ጥፋት እንደሚያደርስ በመረዳት መረዳት ይቻላል።

በታዳጊ አገሮች ያለዉ ሁኔታ ከአውሮፓ በእጅጉ የተለየ ነዉ። ቅኝ ገዥዎች በአፍሪካ ዉስጥ ያላቸዉን ስልጣን ለማስጠበቅ ህዝቡን እርስ በርስ በጎሳ እንዲከፋፈል በማድረግ ፖለቲካዊ ትርጉም ያልነበራቸዉን የቋንቋ ልዩነቶች በማራገብ ህዝቡን የጎሪጥ እንዲተያይ በማድረግ ያልተቋረጠ ግጭት እንዲፈጠር አድርገዋል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ቤልጅየም በሩዋንዳ የፈፀመችው የዘር መከፋፈል ነዉ። አንድ ቋንቋ የሚናገሩትን የሁቱና የቱትሲ ጎሳዎች አንዱን የበላይና ሌላዉን የበታች አድርጎ በማቅረብ እርስ በርስ እንዲቃቃሩ በማድረግ በመጨረሻ ለተፈፀመዉ የሩዋንዳ ዘር ማጥፊት ወንጀል ምክንያት ሆነዋል። በ 1994 ዓም በሩዋንዳ ከተፈፀመዉ የዘር ማጥፋት ወንጀል በሁዋላ ሩዋንዳ ዉስጥ ማንም ሰዉ ሌላዉን ጎሳህ ምንድን ነዉ ብሎ እንዳይጠይቀዉ በመከልከሉ አገሪቱ ብሄርን መሰረት ካደረገ ጥላቻና ግጭት ነፃ ሆናለች። በሌሎች የአፍሪካ አገሮችም ቅኝ ገዥዎች ያመጡትን የዘር መከፋፋል በማስወገድ ማንኛዉም የዘር ጥላቻን መሰረት አድርጎ በንብረት ወይም በሰዉ ላይ የሚፈፀም የጥላቻ ወንጀል ተደርጎ ይቆጠራል። [21] የብሄር ፖለቲካ የሚያመጣዉን ጠንቅ በመረዳት ብዙዎች የአፍሪካ አገሮች በህገ መንግስታቸዉ በዘር ወይም በሃይማኖት ላይ የተመሰረት የፖለቲካ አደረጃጀትንም ከልክለዋል።

## 3. የብሄር ፖለቲካ የጥላቻ ንግግር በኢትዮጵያ

ጥንታዊ ሃገረ መንግስት የነበራትና ብቸኛዋ በአዉሮፓዉያን ቅኝ ያልተገዛችዉ ኢትዮጵያ ደግሞ በተቃራኒዉን ዘርን መሰረት ባደረገ ፖለቲካ ተጠላልፋ ህልዉናዋ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ይገኛል። በሰኔ 2019 የወጣዉ የሎስ አንጀለስ ታይምስ ጋዜታ እንደዘገበዉ ኢትዮጵያ በአገሪቱ በተፈጠረዉ ዘርን ማዕከል ባደረገ ጥቃት ወደ ሶስት ሚልዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ከቀያቸዉ እንደተፈናቀሉ ገልጿል። ይህም ሁኔታ አገሪቱን በተፈናቃዮች ቁጥር በአለም አቀፍ ደረጃ ግንባር ቀደም እንድትሆን አድርጓታል። የዚህ መፈናቃልና ስደት ብቸናው ምክንያት አገሪቱ ለአለፉት 28 አመታት ተግባራዊ ያዳረገችዉ ዘርን መሰረት ያደረገዉ የፖለቲካ ስርአት መሆኑ ግልፅ ነዉ።

በተማሪዎንች እንቅሳቅሴ በ 1960ዎቹ ወደ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ብቅ ያለዉ የብሄር ፖለቲካ ከጅምሩም በጥላቻ የተወለደ ነዉ። ማርክሲዝምንም ሆነ የአገሪቱን ታሪክ ያልተገነዘቡት የዩንቨርስቲ ተማሪዎች የኢትዮጵያ ችግር 'የብሄር ጭቆና ነዉ' በሚል በወስዱት አቋም ባለፉት 50 አመታት የአገሪቱን ፖአቲካ ትርምስ ዉስጥ ከቷታል ። በተለይ ህወሃት፥ ሻእብያና ኦነግን የመሳሰሉት የብሄር ድርጅቶች 'አማራ ጨቁኖናል' በሚል ተንሳስተዉ ተከታዮቻቸዉ ፀረ አማራ አስተሳሰብ እብዲኖራቸው በማድረግ አማራዉ ማህበረሰብ በሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች እንደ ጠላት እንዲያታይ አድርገዉታል። በተለይም ህወሃት በ1968

---

[21] The FBI has defined a hate crime as a "criminal offense against a person or property motivated in whole or in part by an offender's bias against a race, religion, disability, sexual orientation, ethnicity, gender, or gender identity."

ዓም ባወጣዉ የፖለቲካ ፕሮግራም አማራዉ የትግራይ ጠላት እንደሆነ በማስቀመጥ የትጥቅ ትግል አድርጎ የፖለቲካ ስልጣን በመያዝ የጥላቻ ፕሮግራሙን ወድ ተግባር የሚቀይርበት እድል አግኝቶ አማራዉ በገዛ አገሩ እንደ ጠላት የሚታይበት ስርአት ላለፉት 28 አመታት ተግባራዊ ተደርጓል።

ይህ ስርአት በ 1983 ዓም ከተደረገዉ ህወሃት መራሹ የሽግግር ሂደት ጀምሮ አማራዉን ያገለለና አማራን እንደ ጠላት የሚቆጠር ህገ መንግስት ቀራጾ የህዋሀትን ማኒፌስቶ ተግባራዊ አድርጓል። ህውሃት በጠራዉና በሰኔ 1983 ዓም በተካሄደው የሽግግር መንግስት ጉባኤ ሁሉም ብሄረሰቦች ከሞላጎደል ሲወከሉ አማራዉ ግን ሆነ ተብሎ እንዲገለል ተደርጓል። ህወሃት ህገ መንግስት ወደ ማርቀቅና ማፅደቅ ሂደት ሲገባም አጠቃላይ ውይይቱና ቅኝቱ አማራውን በማግለልና በአማራ ጥላቻ ላይ ያተኮረ ነበር። የህገ መንግስቱ መግቢያ እንደሚስረዳዉ የህገ መንግስቱና የፌዴራል ስርአቱ ዋና ግብ 'በታሪካችን የወረስነዉን የተዛባ ግንኙነት በማረም' ላይ ያተኮረ ነዉ በሚል አማራዉ በቀደመዉ ዘምን የተለየ ጥቅም እንደነበረዉ በማስመሰል የተቀመጠው መርህ ህገ መንግስታዊ ስርአቱ አንድን ብሄር ለማትቃት የተዘጋጀ ሰነድ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ።

ህገ መንግስቱ ከመውጣቱ በፊት የህዋሀት ማኒፌስቶን መሰረት በማድረግ አማራን ሊጎዳ በሚችል መልኩ አገሪቱ በዘር እንድትሸነሸን ከመደርጉም በላይ በህገ መንግስት የዘር ፓለቲካን በመፍቀድ አሁን ላለልበት መስቀለኛ መንገድ ዳርጎናል። በተለይ በመላ የአገሪቱ ክፍሎች ተበትኖ የሚኖረዉን የአማራ ማህበረሰብ በሚጎዳ መልኩ የተካለለው የክልሎች ድንበር አማራዉ በገዛ አገሩ ሁለተኛ ዜጋ ሆኖ እንዲኖር አድርጎታል። ክልሎቹ ሲካለሉ አማራው ወኪል ስላልነበረዉና ህወሃት አማራዉን ለመበቀል በውሰደው እርምጃ በአማራ እርስትነት የሚታወቁት አካባቢዎች እንዲውሰዱበት ተድርጓል። ባለፉት 28 አመታት አማራዉ ከተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች እንዲባረርና እንዲሰደድ ተደርጓል። ህወሃት አማራዉን ከፖለቲካና ኤኮኖሚያዊ መዋቅሮች በማባረር የበይ ተመልካች አድርጎታል። የአማራ ክልል ተብሎ በተዋቀረዉ አካባቢ የልማት ስራዎች እንዳይሰሩ በማድረግ ህቡን የማቆርቆዝ ስራዎች ተሰርተዋል። የማራዉን ሃብት ህውሃት ያለከልካይ በመዝረፍ የትግራይ ክልልን ለማልማት ተጠቅሞበታል። ህውሃት ፖአቲካዉን፥ ደህንነትና መከከላከያዉን በመቆጣተር የአንድን ዘር የበላይነት ለማረጋገጥ ከፍተና ጥረት አድርጓል።

እንዲህ ስር የሰደደ መዋቅራዊ ችግር ባላበት አገር የጥላቻ ህግ ማዉጣት ያለዉን ችግር ምን ያህል ሊቀርፈዉ ይችላል የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉን ጥላቻና ግጭት ለማስወገድ የመጀመርያዉና ዋናው ህገ መንግስታዊ ስርአቱ ዘርን መሰረት አድርጎ የተዋቀረዉን በሌላ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መተካት ነዉ። የስርአቱ መሰረታዊ መዋቅር እስካልተስተካከለ ድረስ እንደ ሰደድ እሳት እየተቀጣጣለ ያለዉ ጥላቻና ግጭት የጥላቻን ህግ በማዉጣት አይፈታም ። ስለዚህ መንግስት ቅድሚያ ሊሰጠዉ የሚገባዉ ይህ አንድን ብሄር በጠላትነት በመፈረጅ የተቋቋመዉን ህገ መንግስት ማሻሻልና የዜጎች መብት በእኩልነት የሚያስተናግድ የፖለቲካ ስርአት መፈጠር ላይ ነዉ።

## 4. የጥላቻ ንግግር ህግ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ላይ የሚያመታዉ ተፅዕኖ

ተግባራዊ እንዲሆን የታሰበዉ የጥላቻ ህግ በአገሪቱ ያለዉን ዉሱን ሃሳብን በነፃነት የመግለፅን መብት የበለጠ ሊያዳክመዉ እንደሚችል ስጋት አለ ። በ1987 ዓም ባወጣዉ ህገ መንግስት በአንቀፅ 29 ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት የተረጋጋጠ ቢሆንም ላለፉት 28 እንደታየዉ ሃሳብን የመግለፅ መብት ሙሉ በሙሉ ተገድቦ ቆይቷል። ህወሃት ስልጣን እንደያዘ በርካታ ጋዜጦችና መፅሄቶች በብዛት ይታታሙ ነበር። ነገር ግን መንግስት በህገ መንግስቱ ያስቀመጠዉን ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ ነፃነት ወድ ጎን በመተዉ በትቂት አመታት ዉስጥ ሁሉንም የግል ጋዜጦች በመዝጋት በመንግስት ሚድያዎች ብቻ ፕሮፓጋንዳ እንዲያስተላልፉ ይደረግ ነበር ።

በተለይም የ1997 ምርጫ ተከትሎ የፖለቲካ ምህዳሩ ሙሉ በሙሉ በመዘጋቱ ዜጎች ሃሳባቸዉን መግለፅ አይደለም አገዛዙን ያልደገፉ ዜጎች ሰርቶ የመኖር መብታቸዉን ሳይቀር አደጋ ዉስጥ ወድቆ ነበር።[22] መንግስት ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን ለመገደብ በርካታ አፋኝ ህጎችን አዉጥቶ ተግባራዊ አድርጓል። ከነዚህ አፋኝ ህጎች ዋና ዋናዎቹ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ህግ፥ የፕሬስና የመረጃ ነፃነት መብትና የፀረ ሽብር ህግ ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ። በተለይም በ 2001 ዓም የወጣዉ የፀረ ሽብር ህግ ሃሳብን የመግለፅ መብትን ሙሉ በሙሉ በመገደብ የፖለቲካ ምህዳሩና ኢኮኖሚዉ ሙሉ በሙሉ በአገዛዙ ቁጥጥር ስር እንዲወድቅ ተደረገ። የሽብርተኝነትን ትርጉም አለአግባብ በመለጠጥ ህጋዊ የፖለቲካ ተቃዉሞንና ሃሳብን በነፃነት መግለፅን እንደ ሽብርተኛ በመቁጠር በርካታ የፖለቲካ መሪዎችና አባላት፥ ጋዜጠኞችና የሙብት ታጋዮች ወህኒ እንዲወርዱ ተደርጓል። [23] ዶ/ር አብይ ወደ ስልጣን ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ይህንን የፀረ ሽብር ህግ ለማሻሻል ሂደቶች ተጀምረዋል ቢባልም ሰኔ 15, 2011 ዓም የተከሰተዉን ግድያ ተከትሎ በርካታ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች፥ ጋዜጦችና የፖለቲካ ፓርቲዎች በአለም አቀፍ ደረጃ በተወገዘዉ የፀረ ሽብር ህግ ክስ ቀርቦባቸዋል። ይህ አካሄድ ስርአቱን ለ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ያለዉን ቁርጠኝነት ጥያቄ ዉስጥ አስገብቶታል። [24] መንግስት ለስልጣኑ ያሰጉኛል ያላቸዉን የፖለቲካ ቡድኖች ለማጥቃት የፀረ ሽብር ህጉንና ሌሎች መደበኛ ህጎችን የሚጠቀም አገዛዝ ሊወጣ የታሰብዉን የጥላቻ ህግ ተቃዋሚዎችን ለማጥቃት ሊጠቀምበት እንደሚችል ያሳያል።

በተለይም ስልጣን ላይ ያለዉ መንግስት ሁሉንም የተቃዋሚ ሃይሎች በእኩል ዓይን እንደማይመለከት የሚያሳዩ ሁኔታዎች እየተበራከቱ መምጣታቸዉ የጥላቻ ህጉን የተወሰኑ የፖለቲካ ሃይሎችን ለይቶ ለማጥቃት እንደሚያዉለዉ አመላካች ነዉ። ይህንን ጥርጣሬ የሚያጠናክረዉ ባለፈዉ አንድ አመት የተካሄደዉ የፖለቲካ ለዉጥ አቅጣጫ የሌለዉ፥ ተቋዋማዊ ለዉጡ አስተማማኝ ያልሆነና የኦሮሞ አክራሪ ብሄርተኞች በተረኝነት ስም ፈላጭ ቆራጭ የሆኑበት ስርአት እየተፈጠረ መሆኑ ነዉ።

---

22 https://freedomhouse.org/report/countries-crossroads/2007/ethiopia

23 Ethiopia: Stop Using Anti-Terror Law to Stifle Peaceful Dissent,https://www.hrw.org/news/2011/11/21/ethiopia-stop-using-anti-terror-law-stifle-peaceful-dissent

24 Ethiopia Is at a 'Very Critical Juncture'https://foreignpolicy.com/2019/06/24/ethiopia-is-at-a-very-critical-juncture-abiy-bahir-dar/

ዶ/ር አብይ ኢትዮጵያዊነትንና አንድነትን ቢሰብኩም ዋና ዋና የስልጣን ቦታዎች በአንድ አካባቢ ሰዎች እየተያዘ እንደሆን በመታየቱ የህዝብ ቅቡልነታቸዉን በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ አድርጓል ። አሁንም ስልታዊ በሆነ ሁኔታ ዋና ዋና የፍትህ ተቋማት በኦዴፓ ሰዎችና የዶ/ር አብይ የቅርብ ወዳጆች የተያዙ መሆናቸዉ የጥላቻ ህጉን በመጠምዘዝ ለፈለጉት አላማ ሊያዉሉት የሚችሉበት እድል ከፍተኛ ነዉ።

ከዚህም በተጨማሪ የህወሃት ስርአት የሚመራባቸዉ ፀረ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰቦችና አደረጃጀቶች አሁንም ስራ ላይ ባሉበት ሁኔታ የጥላቻ ህጉ ቀደም ሲል የፀረ ሽብር ህጉ በመንግስት ላይ የሚደረጉትን ተቃዉሞዎች ለማዳፈን ጥቅም ላይ እንደዋለ አሁንም ለተመሳሳይ አላማ የማይዉልበት ምክንያት አይኖርም። ህወሃት ያቋቋማቸዉ ህገ መንግስታ ተቋማት ባልተለወጡበት ሁኔታና ተቃዋሚ ሃይሎችን ለማጥቃት ስራ ላይ እየዋሉ መሆኑ ሲታይ የጥላቻ ህጉን ተግባራዊ ማድረግ በተለየ መልኩ ስርአቱን የሚቃወሙ ሃይሎችን ለማጥቃት ስራ ላይ እንደሚዉል እርግጠኛ መሆን ይቻላል። ስለዚህ ይህ ህገ መንግስትና ጨቋኝ ተቋማት በተገቢዉ መልኩ ተሻሽለዉ በገለልተኛ ተቋማት ሳይተኩ ይህንን የጥላቻ ንግግር ህግ ተግባራዊ ማድረግ ላለፉት 28 አመታት የቀጠለዉን ፀረ ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ በአዲስ መልኩ ለማክናወን የታሰብ አዲስ እቅድ ተደርጎ ሊታይ ይችላል።

## 5. ረቂቅ የጥላቻ ንግግር ህጉ ያሉበት ክፍተቶች

በጠቅላይ አቃቢ ህጉ አማካኝነት የተሰራጨዉ ረቂቅ የጥላቻ ንግግርና  የሃሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከል የወጣ አዋጅ ህጉን ለማወጅ ያስፈለገበትን ምክንያት ሲያስረዳ የጥላቻ ንግግርና የሃስተኛ መረጃ ስርጭት የሚያስከትሉት ግጭትና ጉዳት ለእኩልነት፣ለሰላም፣ ለዲሞክራሲና ለሕዝቦች አንድነት ትልቅ ጠንቅ በመሆኑ ይህንን ለማስቆም አላማ ያደረገ መሆኑን ያትታል። በረቂቅ ህጉ ላይ እንደተገለፀዉ የጥላቻ ንግግር ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ እንደሆነ ምንም አጠያያቂ አይደለም። ነገር ግን የጥላቻ ንግግርን  ለመቆጣጠር የተለየ ህግ ማዉጣት ያስፈልጋል ወይ የሚለዉ አንዱ ጥያቄ ነዉ። በኢትዮጵያ ህግ ዘርን፣ ሃይማኖትንና የፖለቲካ አመለካከት መሰረት ያደረገ ጥላቻ በወንጀል ህጉ የተከለከለ ነዉ።[25] ህዝብን በማንኛዉም መንገድ ወደ ግጭት የሚመሩ ንግግሮችና ድርጊቶች በኢትዮጵያ ህግና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸዉ አለም አቀፍ ስምምነቶች የተከለከሉ ድርጊቶች ናቸዉ።[26] ምንም እንኳን በማህበራዊ የትስስር መድረኮች የሚተላለፉትን የጥላቻ ንግግሮች ለመቆጣጠር ራሱን የቻለ ህግ ማስፈለጉ ቢታወቅም መንግስት የጥላቻ ንግግርን መቆጣጠር ከፈለገ በስራ ላይ ያሉትን ህጎች ተጠቅሞ ህግና ስርአትን በማስከበር ረገድ ብዙ እርቀት መሄድ ይችል ነበር። ያሉትን የህግ ድንጋጌዎች ተጠቅሞ የጥላቻ ንግግርን ለማስወገድ ጥረት

---

[25] የኢፌድሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 29(6) ፥ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ 486

[26] Article 20 (2) of the International Covenant on Civil and Political Rights (ICCPR) states: Any advocacy of national, racial or religious hatred that constitutes incitement to discrimination, hostility or violence shall be prohibited by law.

Article 4, International Convention on the Elimination of Racial Discrimination, 1965 States “shall declare an offence punishable by law all dissemination of ideas based on racial superiority or hatred, incitement to racial discrimination, as well as all acts of violence or incitement to such acts against any race or group of persons of another colour or ethnic origin, and also the provision of any assistance to racist activities, including the financing thereof”

በማድረግ ተቋማትን ማጠናከርና አቅሙን መፈተሽ ሲገባዉ በቀጥታ አዲስ ህግ ወደ ማርቀቅ መሄዱ ምን ያህል ዉጤታማ ሊሆን ይእላል የሚል ጥያቄ ያስነሳል።

ሌላዉ ስጋት በረቂቅ ህጉ ዉስጥ የሚታዩት ክፍተቶች ናቸዉ። ረቂቅ ህጉ የጥላቻ ንግግርን ሲተረጉመዉ የሌላን ግለሰብን፤ የተወሰነ ቡድንን ወይም ማህበረሰብን ብሄርን፤ ሀይማኖትን፤ ቀለምን፤ ጾታን፤ አካል ጉዳተኝነትን፤ ዜግነትን፤ ስደተኝነትን፤ ቋንቋን፤ ዉጪያዊ ገጽታን፤ መሰረት በማድረግ ፣ሆነ ብሎ እኩይ አድርጎ የሚስል፤ የሚያንኳስስ፤ የሚያስፈራራ፤ መድልዎ እንዲፈጸም፤ ወይም ጥቃት እንዲፈጸም የሚያነሳሳ ንግግር ነው በማለት ይገልፀዋል።[27] ይህ አገላለፅ እጅግ ለትርጉም የተጋለጠና ቀደም ሲል የፀረ ሽብር ህጉን በመጠምዘዝ ሃሳብን በነፃነት መግለፅ መብትን ለመደፍጠጥ በቀላሉ ጥቅም ላይ መዋል የሚችልበትን እድል ሊፈጥር  ይችላል። በአዋጁ' እኩይ አድርጎ ማቅረብ፥ ማንኳሰስ' ማለት ምን ማለት ነዉ? መንግስታዊ ስርአቱ ዘርን መሰረት አድርጎ በተዋቀረበት አገር አንዱ ብሄርን ማንኳሰስ ብርቅ ነው ወይ? አማራዉ 28 አመታት ሙሉ በመንግስት ደረጃ ነፍጠኛና ትምክህተኛ እየተባለ ሲንኳሰስ አልነበረም ወይ? አሁንስ እየተንኳሰሰ አይደለም ወይ? ይህን ስርአት እንዲቀትል እየፈለጉ ብሄርን የሚያንንኳስስ ንግግር እንዴት ህገ ወጥ ማድረግ ይቻላል? አንድን ግለሰብ ወይም ቡድን ' እኩይ አድርጎ ማቅረብ፥ ወይም ማንኳሰስ' ትችት ከማቅረብ በምን ይለያል? ማነዉ አንድን ድርጊት ' እኩይ አድርጎ ማቅረብ ወይም ማንኳሰስ' ነዉ ብሎ ብይን የሚሰጠዉ? ይህንን ስራ በብቃትና በገለልተኛነት ሊወስን የሚችል ፖሊስ፥ አቃቢ ህግ ወይም ፍርድ ቤት አለ ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችን ያስነሳል። እንደተለመደዉ ስልጣኑን የተቆጣጠሩት  መሪዎች ይህንን ህግ አምርረዉ የሚተቹዋቸውን ተቃዋሚዎች ለመምታት ሊጠቀሙበት የመቻላቸዉ እድል ከፍተኛ ነዉ።

በረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 4 እና 5 የጥላቻ ንግግርንና የሃሳት መረጃን አስመልክቶ የተገለፀዉ የበለጠ ስጋትን የሚጭር ነዉ። አንቀፅ 4 የጥላቻ ንግግርን አስመልክቶ ሲያስቀምጥ 'ሆነ ብሎ የሌላን ግለሰብን፤ የተወሰነ ቡድንን ወይም ማህበረሰብን ብሄርን፤ ሀይማኖትን፤ ቀለምን፤ ጾታን፤ አካል ጉዳተኝነትን፤ ዜግነትን፤ ስደተኝነትን፤ ቋንቋን፤ ዉጪያዊ ገጽታን፤ መሰረት በማድረግ ፣ እኩይ አድርጎ የሚስል፤ የሚያንኳስስ፤ የሚያስፈራራ፤ መድልዎ እንዲፈጸም፤ ወይም ጥቃት እንዲፈጸም የሚያነሳሳ ጥላቻ አዘል መልእክቶችን በመናገር፤ ፅሁፍ በመፃፍ፤ ምስል፤ ስእል፤ የኪነጥበብ እና እደ ጥበብ ውጤት፤ የድምጽ ቅጂ ወይም ቪድዮ በማተም፤ በማሳተም ወይም በማሰራጨት፤ መልእክቶችን ብሮድካስት ማድረግ ወይም በማህበራዊ ሚዲያ ማሰራጨት፤ ወይም በሌሎች ማናቸዉም መገናኛ መንገዶች ለህዝብ መልእክቱ እንዲደርስ ማድረግ ክልክል ነው ' ይላል።

ከፍ ሲል እንደተገለፀዉ ይህም ክፍል እጅግ ሰፊና ለትርጉም በቃላሉ የተጋልጡ አባባሎችን የያዘ ነዉ። ብሄርን ፥ ሃይማኖትን፥ ፆታን፥ ቋንቋን መሰረት በማድረግ የሚቀርቡ ትችቶችን በቀላሉ በዚህ አንቀፅ መሰረት የጥላቻ ንግግሮች ናቸዉ በሚል ክስ ለማቅረብ ያስችላል። በተለይ ሁሉም ወገን በብሄር ተደራጅቶ ዳርና ዳር ቆሞ በሚሰዳደብበትና አገሪቱን ለሚንጣት የጎሳ ፖለቲካ ፖለቲካዊ መፍትሄ ባልተቀመጠበት በዚህ  ወቅት እንዲህ አይነት ህግን በማዉጣት የጥላቻ ንግግር እቆጣጠራለሁ

[27] በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጥላቻ ንግግርና የሃሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከል የወጣ አዋጅ፥ አንቀፅ 2(2)

ማለት የማይቻልና ይልቁንም በቀላሉ መንግስትን የሚቃወሙትን ለማጥቃት ስራ ላይ ሊዉል የሚችል አንቀፅ ነዉ። በተለይም ይህ አንቀፅ በማህበራዊ ሚድያ የሚደረጉትን የሃሳብ ልዉዉጦች ለመቆጣጠር ያለመ እንደሆነ ግልፅ ነዉ።

አዋጁ በአንቀፅ 5 የሚደነግገዉ የሃሰተኛ መረጃ አንቀፅም ሃሳብን የመግለፅ መብትን የሚገድብ ነዉ። ይህ አንቀፅ 'የፍሬ ነገር ወይም አንኳር ይዘቱ ውሸት መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው፣ ሁከት ወይም ግጭት የማስነሳት፣ ወይም ጥቃት እንዲደርስ የማድረግ እድሉ ግልጽ በሆነ መልኩ ከፍ ያለ መረጃን ሆነ ብሎ በማንኛውም መንገድ ማሰራጨትና ለህዝብ እንዲደርስ ማድረግ የተከለከለ ነው' ይላል ። መረጃ በፈጠን መንገድ በሚተላልፍበት በዚህ ዘመን አንድ ሰዉ የሚያሰራጨዉ መረጃ እዉነት አለዉ ብሎ ያመነበት ከሆነ ከማሰራጨት ሊገደብ አይገባም። ይህንን ሁኔታ ለመቆጣጠርም እጅግ አዳጋችም ነዉ። ማህበራዊ ሚድያዉ በአለም አቀፍ ደረጃ የሃሰት መረጃን በማሰራጨት የሚነቀፍ መሆኑ ቢታወቅም ችግሩ ግን የሚቀረፈዉ ግልፅ እና ተጠይቂነት ያለው የመንግስት አሰራርና ተቋማት በመገንባት ነዉ። የመንግስት አካላት ተጠያቂነት ሳይኖራቸዉና ራሱ መንግስት የሃሰት መረጃን በሚያሳራጭበት አገር ህዝብን ለማፈን የሚደረግ እንቅስቃሴ በቋፍ ያለዉን የአገሪቱን ሁኔታ የበለጠ ሊያባብሰው ይችላል ። የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት የሆነዉ የሂማን ራይትስ ዋች ( Human Rights Watch) በቅርቡ ለቂቅ የጥላቻ ንግግር ህጉን አስመልክቶ ባወጣዉ መግለጫ እንደገልችፀዉ ሊወጣ የታሰበው ህግ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን ሊጎዳ እንደሚችልና የጥላቻ ንግግር ለመቆጣጠር የተሻለዉ አካሄድ ህዝብን ማስተማርና መንግስት ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ሲያዳብር መሆኑን አስገንዝቧል። [28]

## ማጠቃለያ

የጥላቻ ንግግር በኢትዮጵያ ዉስጥ ባለዉ የፖለቲካ ሁኔታ የተነሳ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰና ከፈተኛ ችግር እየፈጠረ ይገኛል። ከዚህ አንፃር መንግስት በስራ ላይ ያሉትንም ሆነ አዳዲስ ህጎችን በማዉጣት ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት ቢያደርግ ክፋት የለዉም። ነገር ግን በአገራችን ሁኔታ የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል ምን አይነት መፍትሄ ያስፈልጋል የሚለዉ ትልቅ ትኩረት የሚጠይቅ ጉዳይ ነዉ። በቅርቡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጥላቻ ንግግርን ለማስወገድ ባወጣዉ የድርጊት መርሃ ግብር መሰረታዊ መፍትሄዎችን ያስቀምጣል። [29] የመንግስታቱ ድርጅት የድርጊት መርሃ ግብር የጥላቻ ንግግርን ለማስወገድ ትልቅ ትኩረት የሰጠዉ የጥላቻ ንግግር ዋናዉ መነሻ ምክንያትና የሚያባብሱትን ሁኔታዎችን መለየት ነዉ። ይህን ሁኔታ በአገራችን ሁኔታ ስናየዉ አሁን በከፈተኛ ደረጃ እየተስፋፋ ላለዉ የጥላቻ ንግግር ስር መሰረቱ አገሪቱ ባልፉት 28 አመታት የተከተለችዉ ጎሳን መሰረት ያደረገ የፖለቲካ ስርአት መሁኑን ብዙዎች ይስማሙበታል። ይህ ስርአት የብሄር መብቶችን ለማከበር ነዉ የሚል ትርጉም ቢሰጠዉም መነሻዉና መድረሻዉ ግን ጥላቻ ነዉ። ይህንን ህገ መንግስት ተሸክመን የጥላቻ ንግግርን ዋጅ በማዉጣት

---

[28] Tackling Hate Speech in Ethiopia: Criminalizing Speech Won't Solve Problem https://www.hrw.org/news/2018/12/03/tackling-hate-speech-ethiopia

[29] United Nations Strategy and Plan of Actions on Hate Speech, https://www.un.org/en/genocideprevention/documents/UN%20Strategy%20and%20Plan%20of%20Action%20on%20Hate%20Speech%2018%20June%20SYNOPSIS.pdf

እናሶግደዋለ ማለት የዋህነት ነዉ። ስለዚህ የመንግስት ትልቁ ትኩረት ሊሆን የሚገባዉ ይህን ጥላቻን የሚፈለፍል ስርአት ዜጎች በእኩልነት በሚኖሩበት ስርአት መቀየር ካልተቻለ ጥላቻ የማህበረሰቡ ጠንቅ ሆኖ መቀጠሉ የማይቀር ነገር ነዉ።

የመንግስታቱ ድርጅት የጥላቻ ንግግርን ለማስወገድ ሌላዉ ትኩረት ያደረገባቸዉ ጉዳዮች የጥላቻ ንግግር ሰለባዎችን መርዳት፥ የጥላቻ ንግግር የሚያራምዱትን እንዲቀራረቡ ማድረግ፥ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ማስተማርና ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ አሳታፊ አሰራር ማስፈን ናቸዉ። ከዚህ ዝርዝር የጥላቻ ህግን መጠቀም የመጨረሻው አማራጭ እንደሆነ እንረዳለን፡ አገራችንን ከጥላቻና መለያየት ለማዳን ዋናዉ መንገድ ፖለቲካዊና ማህበራዊ መፍትሄዎች ላይ ማተኮር ነዉ። ብሄራዊ እርቅና መግባባት፥ ህብረተሰቡም ማስተማር፥ መንግስታዊ ተቋማት ከአድልዎ ነፃ ማደረግ፥ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለበት ስርአት መገንባት የጥላቻ ንግግርን ለማስወገድ ትልቅ ፋይዳ ይኖራቸዋል። የጣላቻ ንግግር ህግ ማዉጣት በራሱ ችግር ባይሆንም ውስብስብ ከሆነው የአገራችን ሁኔታ አንፃር ይህን ህግ ተግባራዊ በማድረግ ችግሩን ለመፍታት መሞከር ትልቅ ችግር ሊፈጥር ስለሚችል ጥንቃቄ ያስፈልገዋል።